# ሻለቃ ግርማ ይልማ

የአቶ አማረ አፈለ ብሻው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም ነገም የተባለውን አዲስ መጽሐፍ በልዩ የባለቤትነት ስሜት አገራዊ ኩራትና የማንነት አኩሪ ትዝታ አነበብኩት። ደራሲው ስለአጤ ቴዎድሮስ የተፃፉና በቃል የተነገሩ የኢትዮጵያዊና የውጭ የታሪክ ሥራዎችን በብዛት የመጽሐፉ አካል በማድረግ የመረጡት የአቀራረብ ዘዴ ይበል የሚያሰኝ ነው። እጅግ በጣም ብዙ የሆኑትን ስለአጤ ቴዎድሮስ የተጻፉትን የታሪክ ሰነዶች ለማንበብ በቂ ጊዜ ለሌላቸው የአቶ አማረ አፈለ ብሻው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም ነገም ምጥን ምግብ ነው።

ደራሲው ይሄንን መጽሐፍ ለማቅረብ ያደረጉትን ጥረት ከራሳቸው እንስማ *"በኢትዮጵያዊያን የተጻፉት የኢትዮጵያን ታሪክ በክፉም በደጉም የሚያነሱትን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት። እራሴን አንቱ ለማሰኘት ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያውቀው ከ1000 በላይ መጻሕፍትን፤ ከ200 የሚበልጡ መጽሔቶችንና ጋዜጠኞችን፤ የሰእል ድምፅ ቪዲዮችንና ካሴቶችን አጠራቅሜ ሳነብና ስመለከት ይች ጎሰቋላ የአጤ ቴዎድሮስና የእኛ አገር ትዝ ትለኛለች። ስለአገሬ ጠዋትና ማታ አሰባለሁ"።* የእናታችውንና የፍቅረኞቻቸውን ደብዳቤ ለምንበብ ጊዜ የላቸውም እየተባልን በምንታማ ዜጎች መካከል የአቶ አማረ የመጽሐፍት ፍቅርና የንባብ ባሕል በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። በጥቂት ጊዜ ትውውቃችን ከሰበሰቧቸው እጅግ ብዙ መጽሐፍት ጥቂቱን እንዳነብ እድል ስለሰጡኝ ባለውለታዬ ናቸው።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አጤ ቴዎድሮስ ጀግናቸውና በስሜትና በሀሳብ አርአያቸው እንደሆኑ አውቃለሁ። የአጤ ቴዎድሮስን ጎራዴ በአየር እየቀዘፉ የሕዝብና የአገር ክብር ከማይደፈር የአጤ ቴዎድሮስን ጽዋ እንደሚቀምሱ ለሕዝብ በመገናኛ ብዙኃን ቃል እንደገቡ ትዝ አለኝ። የቁርጥ ቀን ሲመጣ በኢሳዴሪ ብሔራዊ የሸንጎ አባል የነበሩ የሃይማኖት አባት ይህንኑ ነበር ያስታወሷቸው። **"የቴዎድሮስን ጽዋ ከመጠጣት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለዎትም"** አሉዋቸው። ፈታኝ እለት ሲመጣ ግን የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት አድናቂዎች፤ አክባሪዎችና ደጋፊዎች በእጅጉ ተሸማቀቅን። ሕዝብና አገር ብለን በእውነት ለተነሳን ኢትዮጵያዊያን አጤ ቴዎድሮስ ትላንትም ዛሬም ነገም የአጥቢያ ኮከባችን ናቸው።

የሕዝብና የአገር ክብር እንዳይደፈር አጤ ቴዎድሮስ ስለወሰድዋቸው ቅደመ እርምጃዎች በልጅነቴ የገበየሁት የታሪክ ትምህርት ሁልጊዜ መንፈሴን ያሞቀዋል። ቀላል ግን የሕይወት ዘመን ትዝታ የሚጭረውን ምሳሌ እጠቅሳለሁ። **"ሰንቱን ክርስቲያን ያልሆኑ አገሮችን አልፋችሁ ከእናንተ በፊት ክርስትናን የተቀበለ ሕዝብ ምን አዲስ ነገር ታስተምራላችሁ? ንሳ አለሜ እዚያው ጀልባቸው ድረስ ሸኝልኝ የቅድስት አገሬን ትቢያ ይዘው ከኢትዮጵያ እንዳይወጡ መጨሚያቸውን በሚገባ አራግፍልኝ"** ብለዋል። አጤ ቴዎድሮስ ለመላው ሕዝብና አገር ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ትቢያ የሚሳሱ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ።

የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማና አርቆ አሳቢነት ለመረዳት በንግሥ በዓላቸው ለህዝብ ያደረጉትን ንግግር በጥሞና ማጤን ያስፈልጋል። ንግግራቸውን በአጭሩ እጠቅሳለሁ። ". . . **የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ አንተ ለአቋቋምከው መንግሥትና ለአነገስከው ንጉስ ተገቢውን ግብር እንድትከፍል ሕግ ይወስንብሃል። ይሕ ያቋቋምከው መንግስት አንተንና ኢትዮጵያን እንደሚያገለግልና እንዲጠብቅ ለመለመልከው ነፍጠኛ (ወታደር) ስንቅና ቀለቡን ሳያጓድል እንዲሰፍርለት። ከዚያም ሌላ መተዳደሪያ የሆነ አበል እንዲሰጠው እንጂ እንዳለፈው የመሳፍንት ጭፍራ ዘረፋና ተጽዕኖ እንዳያደርግብህ ያደርጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ከአሁን በፊት ሰትገድል፤ ሰትቀማ፤ ቤት ሰታቃጥል፤ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩትን እህቶችህንና ወንድሞችህን ባሪያ አድርገህ ስትሸጥና ስትገዛ የነበርክ ሁሉ ከአሁን በፊት ስለፈጸምከው ድርጊት ምህረት ተደርጎልሃል። ወደ ቤትህና ወደ ሀገርህ በሰላም ተመልሰህ በግብርናህና በእጅ ሞያህ ተሰማርተህ እንድትኖር ያለፈውን ወንጀልህን ሳላይ የሚመጣውን በማስተዋል ሙሉ ምህረት ተደርጎልሃል።**

**በሸፍትንት ሁነህ የምትቀማና ወንድምህን አድብተህ የምትገድል ባሪያ ብለህ ሰውን የሸጥክና የገዛህ እንደ አውሬ ታድነህ ተይዘህ በአደባባይ እጅህና እግርህ ፈጽሞ እንዲቀረጥ ርሀራሄ እንደማይደረግልህ እወቅ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ትናንትና ከትላንት ወዲያ ባሪያ ብቻ ሳይሆን ለሥልጣንና ሹመት ሲባል ሴት ልጅህን ሸጠሃል። አንተም አንድ ሰትሆን ሁለት ሴት ይዘሃል። ከእንግዲህ ግን ይህ ቃል ተስተካክሎ በሕግ እስቲጸድቅና እስኪታወጅልህ ድረስ እንድታስብበትና እንድትመርጥ ቀን ሰጥቼሃለሁ . . ."** ብለዋል።

እንግሊዞች መቅደላን እንደከበቡ አጤ ቴዎድሮስ መጨረሻቸው እንደደረሰ በማወቅ ለጦር መሪው ለሮቤርት ናፒየር የጻፉላቸው ሁለት ደብዳቤዎች አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ይላሉ። **"የአገሬ ሰው ግብር ሥራዓት ግባ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በሥራዓት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ። ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውዬ ነው። የአገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዟል ሰልሟል እያለ አስሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም መሪ ይስጠው። እርሱ እንደወደደ ይሁን"** ይላል። ሁለተኛው ደብዳቤያቸው ደግሞ አመራራቸው ለምን ኃይለኛ ጭካኔ እንደበዛበትና ጥረታቸው ሁሉ ለምን ከንቱ እንደቀረ ገልጸውታል። **"የአገሬ ሰው ከትዕዛዝ መውጣቱን አይቼ ብገድለው ብቀጣው፤ አልመለስ ቢል፤ ቢነደኝና ብቀና በገዛ ጠበንጃዬ እሞታለሁ ብዬ ሰይጣን አሳብ አሳደረብኝ"** ብለው ጽፈው ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ በጋፋት ያስሩትን መድፍ ሰባስቶፓል ብለው የሰየሙት ሩሲያውያን በክራይሚያ ጦርነት በቱርኮች ላይ የተቀዳጁትን ድል እሳቸውም በግብጾች ላይ የሚደግሙት ስለመሰላቸው ነበር። ግን የተሸነፋት ባልነቃ ሕዝብ ተደናቅፈውና "ባልሰላ መድፍ" መቅደላ ላይ ተዋግተው ብቻ አልነበረም። ብሪታንያና ሌሎች ምዕራባዊ የአውሮፓ አገሮች የሩሲያውን የሰባስቶፓል ድል ቱርኮችን በማገዝ እንዳጨናገፋቸው ሁሉ እነዚሁ አገሮች አጤ ቴዎድሮስ በግብጽ ላይ ድል እንድያገኙ አልፈለጉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በበኩሉ የአጤ ቴዎድሮስን ሞት ተመኘ። አንዱ ወታደር ፈጣሪውን ሲያማርር አጤ ቴዎድሮስ ከኃላው ደርሰው ሰለሰሙት **"ለምን ፈጣሪህን ታማርራለህ?"** አሉት። እርሱም ሲመልስ **"ጃንሆይ አልሰማኝ አለ እንጂ እኔስ ሁልጊዜ ለመንኩት"** አላቸው። ይህ የሁሉም ጸሎት ሆነ! ሕዝቡም እንደፈለገው ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም ለተከፋቸው ሕዝብ ራሳቸውን አስወገዱለት። ችግሩ ግን ተባባስ እንጂ አጤ ቴዎድሮስ ጋር አልተወገደለትም። የችግሩ ምክንያት እርሳቸው አልነበሩምና።

በአጤ ቴዎድሮስ ትጉህና ፈጣን እቅዶች ተዳክመው የነበሩ ጠረኛ መሳፍንት በተዘናጋው ሕዝብ በመጠቀም እንደገና አንሰራሩ። ከድሮው በበለጠ ተጠናክረው ተነሱ። እንደ አጤ ቴዎድሮስ ለደሃ በማያዝኑና በማይራሩ መሳፍንት አገር ተጨነቀች። ሕዝብ መድረሻ አጣ! የአጤ ቴዎድሮስ መነሳት አስደንግጧቸው የነበሩት የውጭ ጠላቶች ይበልጥ ትምህርት ቀስመው በየአቅጣጫው ብቅብቅ አሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሌላ እውነተኛና ታማኝ ዓላማው የማከሽፍበት ቴዎድሮስ የሚመጣበትን ቀን እንደገና በናፍቆት መጠባበቅ ጀመረ።

ለራሳችን፤ ለቤተባችን፤ ለጎረቤቶቻችን፤ ለሕዝባችንና ለአገራችን ሀቀኞችና ታማኞች ካልሆን የግልም ሆነ የጋራ ዓላማዎቻችንን ምንጊዜም ከዳር አይደርሱም። የአጤ ቴዎድሮስ እጣ ፈንታ የእኛም ይሆናል። ዛሬ ስለመልካም ስነ-ምግባር፤ ስለንጹህ ሕሊናና ስለይሉኝታ መወያየት የሚያሳፍር ጊዜው ያለፈበትና ለአደጋ የተጋለጠ እሴት በከንቱ መቶዝም እንደሆነ የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ብቸኛውና ትክክለኛው መንገድ ግን እንደ አጤ ቴዎድሮስ ታማኝ መሆን ነው። ቆንስል ፕላዊዴን ልክ እንደ ዶ/ር መርዕድ ስለአጤ ቴዎድሮስ መልካም ባህሪያት የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል።

*"... ለጋስነታቸው በኢትዮጵያ የመሪዎች ታሪክ ወደር የሌለው ነው። ድል ሲያደርጉ ሆደ ሰፊና መሀሪ መሆናቸውን ከአንደበታቸውና ከተግባራቸው በጥንቃቄ ተመልክቻለሁ። ከመጠን በላይ ለጋስና ከማንኛውም ፍቅረ ንዋይ የጸዱ ናቸው። ድል ያደጓቸውን ሁሉ ከማረኩ በኃላ እንደጠላት ሳይሆን እንደወዳጅ ያዩዋቸዋል። የእምነታቸውም ጽኑነት የሚደነቅ ነው...ብሏል።*

አቶ አማረ አፈለ ብሻው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም ነገም በተሰኘው መጽሐፋቸው መይሳው የሞቱበትን የአንድ መቶ አርባ ሦስተኛ ዓመት ስለ ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ የተሟላ ስብዕና ታላቅ ገጸ በረከት አቅርበውልናል። እግዚአብሔር ይባርካቸው።